# ሸህ ሙሐመድ ሐሰን አል አሙዲ ተወቃሽ ወይስ ተመስጋኝ?
# ተረጋሚ ወይስ ተመራቂ?

በቀደም ቅዳሜ ምሽት አንድ ወዳጀ ደውሎ "የሰይፉ ፋንታሁንን ዝግጅት አዳምጥ የምትጨነቅበትን እንቧጭ አረም ማስወገጃ ማሽን የሚገዛ ባለሀብት ተገኝቶልሀል፡፡ የባለሀብቱን ማንነት ገና አልገለጠም!" አለኝ፡፡ ሬዲዮ (ነጋሪተ ወግ) ከፍቸ ስጠባበቅ ቆየሁና አራት ሰዓት ከምናምን ላይ ሰይፉ ፋንታሁን "የጣናን እንቧጭ አረም የሚያጠፋ ማሽን መግዣ የሚሆን ገንዘብ የሚያበረክቱት ሸክ ሙሐመድ አላሙዲ ናቸው!" ብሎ ማንነታቸውን ገለጸ፡፡ በመሠረቱ የእንቧጭ አረምን የሚነቅል እንጅ የሚያጠፋ ማሽን (ማሳልጥ) በዓለም ላይ የለም፡፡ ሰይፉ አውቆ ለማጋነንና አግባብ ያልሆነ ውዳሴ ለሸሁ ለማሰጠት ፈልጎ ይሁን ተሳስቶ አላውቅም "የሚያጠፋ!" በማለት በሰው ልብ ላይ ያልሆነ ተስፋ እንዲሞላ አድርጓል፡፡ ፈጣሪ የእርኩሱን ወያኔ ዕድሜ ያሳጥረውና ከእንግዲህ እንቧጭ ከጣና መቸም ጊዜ ቢሆን ላይጠፋ ጣናን በክሎታል፡፡ ማድረግ የሚቻለው በበቀለ ቁጥር እየነቀልን ሰፊ ጉዳት እንዳያደርስ ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ ነው እንጅ ከእንግዲህ ምንም ቢደረግ እንቧጭን ከጣና ማጥፋት አይቻልም፡፡

ከዚያ ይሄንን ዜና እንደሰማሁ በማግስቱ ዳንኤል ክብረት እንዳደረገው ምድረ ካድሬ (ወስዋሽ) ይህችን ዜና በማራገብ ለወያኔው ቀኝ እጅ ለሸህ አል አሙዲ ገጽታ ግንባታ በተናበበና በተቀናጀ መልኩ ዜናውን እንደሚያራግቡት ስለገባኝ አንድ ነገር ማድረግ አስቤ ፌስ ቡክ (መጽሐፈ ገጽ) ስገባ ወሬውን ከመቸው ተቀብለው እንደናኙት ያም ያም ያራግበው ይዟል፡፡ ወዲያውኑ መጽሐፈ ገጼ (ፌስ ቡኬ) ላይ የሚከተለውን ማሳሰቢያ ጻፍኩ፡-

"ማሳሰቢያ!

ሸህ አላሙዲን ለጣና የእንቧጭ አረም መንቀያ ማሽን (ማሳልጥ) መግዣ ገንዘብ ሊሰጥ ነው ብላቹህ የድጋፍና የምስጋና መልእክት በየ ፌስ ቡክ አካውንታቹህ (መጽሐፈ ገጽ መዝገባቹህ) እያስተላለፋቹህ ላላቹህ የፌስ ቡክ (የመጽሐፈ ገጽ) ጓደኞቸ፡፡
ምን ያህል አቅለቀላል፣ ተላላና ግብዝ ብትሆኑ ነው ከወያኔ አገዛዝ ጋር ሆኖ ሕዝባችንንና ሀገራችንን ለመከራ የዳረገን ሰው ፍርፋሪ ጣለልን ብላቹህ እንዲህ የምትፈነጥዙት?? ከወያኔ ጋር ቆሞ ከገጠር እስከከተማ ሕዝባችንን እያፈናቀለ ለችግር የዳረገ፣ ሀገራችንን እየዘረፈ እና እያዘረፈ ያለ ዋናው ማን ሆኖ ነው እንዲህ የሚኮነው???
ይሄንን በማድረጋቹህ እንዲህ ዓይነት ተላላ፣ አቅለቀላልና ግብዝ ጓደኛ እንዲኖረኝ አልፈልግምና ከጓደኝነት ሳሰናብታቹህ እያዘንኩ ነው! ደኅና ሁኑ!!
ግልጽ ማድረግ የምፈልገው ነገር አላሙዲን በልገሳ ስም የሚሰጠው ገንዘብ ካለ አንቀበል አላልኩም፡፡ ገንዘባችን ነውና አሳምረን እንቀበላለን! ምስጋናውንና ማሸቃበጡን ግን ምን አመጣው?? የሰረቀኝ ሰው ከሰረቀኝ ንብረት ኢምንቷን ቢመልስልኝ እንዴት ነው ላመሰግነው የምችለው???" ብየ ጻፍኩ፡፡

እናንተየ ሰውን ግን ምን ነክቶታል? ንቃተ ሕሊናችን ይሄንን ያህል ላሽቋል እንዴ ለካ! ተንጫጩብኝ አልኳቹህ! አጠገባቸው ቢያገኙኝ ቀረጣጥፈው በልተውኛል፡፡ የዓለም አቀፍ ገዥ ሕግ "አንባገነን፣ አረመኔያዊና ኢሰብአዊ የዘራፊ ቡድን አገዛዝን ወቃወም ማውገዝ አለመተባበር ግዴታ ነው፣ መርዳት፣ መደገፍ ደግሞ ወንጀል ነው!" ይላል እንጅ የት ቦታ እንዲህ ዓይነቱን አገዛዝ "መደገፍ፣ መርዳት መብት ነው!" እንደሚል አላውቅም ምን አሉ መሰላቹህ "አልአሙዲን ወያኔን መደገፍ፣ መርዳት ከፈለገ መደገፍ መርዳት መብቱ ነው!" ምንንትስ ቅብርጥስ አሉ፣ ስድቡ፣ እርግማኑ ምን ተረባረቡብኝ አልኳቹህ፡፡ አንዳንዶቹ እማ አል አሙዲ ለነሱም ፍርፋሪ እንዲጥልላቸው ለማድረግ ያሰቡ ይመስላሉ፡፡

አያመዛዝኑም ጭፍን ደጋፊው ናቸው፡፡

ለነገሩ የእነዚህን ሰዎች ስሜት ከዚህ ቀደምም አላሙዲን ቆሸ በተባለው ሥፍራ ወያኔ ደማሚት አፈንድቶ በርካታ ወገኖቻችንን ከነሕይዎታቸው ቀብሮ እጅግ ዘግናኝ አደጋ በተፈጠረ ጊዜ በአደጋው ላለቁ ወገኖቻችን ቤተሰቦች ገንዘቡ እስከአሁንም ድረስ ለተጎጂ ቤተሰቦች ባይሰጥም ሸህ አል አሙዲ ከፍ ያለ ገንዘብ እረዱ በተባለ ጊዜ አል አሙዲን ለማመስገን ሽሚያ ተይዞ ሁኔታው እጅግ ቢያቃጥለኝ ለሰዉ "እናንተ ሰዎች እንዴት ነው የምታስቡት? ወገኖቻችን እኮ እዚያ ቆሻሻ ስፍራ ላይ ሔደው ለመስፈር የተገደዱት ለዜጎች ቤት ሠርተው የሚኖሩበት ቦታ በመንፈጉ፣ ቤት ሠርተው ይኖሩ የነበሩትንም እያፈናቀለ ለአል አሙዲና መሰል አጋር ባለሀብቶች እየሰጠ መድረሻ ስላሳጧቸው እኮ ነው፡፡ አገዛዙ ለራሱና ለአጋር ባለሀብቶች ብቻ የሚጠቅም ሀገርንና ዜጎችን ግን የሚጎዳ ፖሊሲ (መመሪያ) አውጥቶ ዜጎች መድረሻ በማጣታቸው፣ ሀገሪቱ የናጠጡ ሀብታሞች ብቻ እንድትሆን በማድረጉ ዜጎች ለእንዲህ ዓይነት አደጋ በመጋለጣቸው ይሄንን አጋጣሚ ኢፍትሐዊው፣ ኢ ሰብአዊና የዜግነት መብት የሆነው የወያኔ ፖሊሲ እንዲቀየርና ዜጎች ድሀም ሆኑ ምን የመኖሪያ ስፍራ የማግኘት ሰብአዊና የዜግነት መብታቸውን የማስከበሪያ ለውጥ እንዲመጣበት ለመጠቀም ማሰብና መንቀሳቀስ ሲኖርብን ለዚህ ችግር የዳረጉንን ባለሀብትና አገዛዙ ይሄን ስለረዳቹህን፣ ያን ስላደረጋቹህልን እያልን ሲቃ እየተናነቀን ለማመስገን መራኮታችን የጤና ነው ወይ? አስተሳሰባችን የዚህን ያህል ዘግጧል ማለት ነው? ወዳጅ ጠላትን ለይተን አናውቅም ማለት ነው? በዚህ ዓይነት እንዴት ነው ልንነቃና ለለውጥ ልንነሣሣ የምንችለው? እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎችን በመጠቀም መብታችንን ለማስከበር እኛው እራሳችን ለራሳችን ካልታገልን ማን ሊታገልልን ነው? ወያኔ እንዲህ ዓይነት ከገጠር እስከከተማ ዜጎችን ሰብአዊና የዜግነት መብት አልባ የሚያደርግ ፖሊሲ (መመሪያ) ሥራ ላይ ያዋለው እኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድሀ ካልሆነና የመሬት ባለቤትነት መብት አልባ ካልሆነ ወይም የመሬት ባለቤትነት መብቱን ካልተነጠቀ በስተቀር እንደፈለጉ እያፈናቀሉ የመግዛት፣ የመበዝበዝ ዕድል እንደማይኖራቸው ስለሚያውቁ እኮነው፡፡ ኧረ መቸ ነው የምንነቃው? እንዲህ ዓይነቱ አደጋና መከራ እንኳ አያነቃንም እንዴ? ይሄ አደጋ በሌላ ሀገር ቢሆን እኮ መሬት አንቀጥቅጥ ዐመፅ ይቀሰቅስ ነበረ እኮ…." እያልኩ እየተራገምኩ ሁሉ ስለጉዳዩ ለጻፍኩት ጽሑፍ ከተሰጠው ምላሽም ዓይቸው ነበረ፡፡

አሁን ደግሞ ይሄንን ከላይ ያነበባቹህትን ሲያዩ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች አበዱብኝ አልኳቹህ፡፡ እጅግ በጣም የገረመኝ ደግሞ ካበዱብኝ ግለሰቦች መሀከል እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ይኖራቸዋል ብየ የማልጠብቃቸው ግለሰቦችም መገኘታቸው ነው፡፡ ሦስቱን ለምሳሌ ያህል ባነሣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የጀርመን ነጋሪተወግ (ራዲዮ) የአማርኛው ክፍል ዘጋቢ የሆነው ጋዜጤኛ ነኝ ባይ ነቢዩ ሲራክ፣ ጠበቃ መምህርና ገጣሚ ነኝ ባዩ መንግሥቱ ዘገየና ሌሎች የኮሌጅ መምህራን ነን የሚሉ ይገኙበታል፡፡

የሚገርመው መንግሥቱ ገዘየ በተመላለስነው አስተያየት የአስተሳሰቡን አለመብሰል በመረዳቱ አፍሮ ነው መሰለኝ አጥፍቶታል፡፡ እስኪ የፕሮፌሰር መስፍንን አጭር አስተያየት ላስነብባቹህ "ወሬ ቀላል ነው፤ ጀግናም ያስመስላል፤ ሰረቀ የምትለውን ሲሰርቅ አላስጣልህም! ሲሰጥ ምላስን መሳል ጥቅሙ ምንድን ነው?" ይላል፡፡ እንዲህም ብየ መለስኩላቸው "ማስጣል ያለማስጣሉ ጉዳይ በአንድና በሁለት ሰው የሚሆን እንዳልሆነ ያውቃሉ ብየ እገምታለሁ፡፡ ግን አልአሙዲ ለምን የሚሰጥ ይመስልዎታል ፕሮፌሰር?" ብየ፡፡ መልስ ይሰጡኛል ብየ ለሦስት ቀን ብጠብቃቸውም መልስ ሊሰጡኝ አልቻሉም፡፡ ብዙ ልላቸው የፈለኩትን ነገር ነበረ አመለጡኝ፡፡

ወገኖቸ ንቃተሕሊናችን የዚህን ያህል ደካማ ሆኖ ታዲያ በዚህ የንቃተ ሕሊና ደካማነታችን ወያኔ በባዕዳን አማካሪዎቹ እየተመከረ በተደጋጋሚ እንደሚያደርገው እንደፈለገ የሚያጃጅለን አድርጎ አስቦ ቢንቀንና ማጃጃሉን ቢቀጥል ይፈረድበታል ታዲያ? አልአሙዲ፣ ሌሎች የወያኔ አጋር ባለሀብቶችና ወያኔ ምንና ምን ሆነው ሁሉንም ነገር ከሕዝብ ነጥቀው ሀገሪቱን የብቻቸው አድርገው ይሄንን ሕዝብ አደህይተው እየተጫወቱበትና በባርነት እየገዙት እንደሆነ ቢያንስ በእነኝህ ሰዎችና በነሱ ደረጃ ባሉ ሰዎች ዘንድ እንዴት ግንዛቤ አይያዝም? ዜጎች የሀገራቸው የመሬታቸው ባለቤትና ባለመብት ቢሆኑና ለድህነት ባይዳረጉ ኖሮ በማንም እየተፈናቀሉ መድረሻ ማረፊያ አጥተው ቆሻሻ ላይ ይወድቁ ነበረ ወይ? ጣናን ያክል የሀገር ሀብት ለአደጋ ሲጋለጥ የሚደርስለት መንግሥት አጥቶ፣ እራሱም አቅም አልባ ሆኖ ክብሩን በእጅጉ የተዳፈረውንና የጠላቱን የወያኔን ቀኝ እጅ ግለሰብ ለመማጸን ይዳረግ ይገደድ ነበረ ወይ? ይሄንን ሕዝብ

ልናስተምረው የሚገባን በአገዛዙና በአጋሮቹ በሚፈጠሩ ችግሮች ለጉዳትና ለአደጋ ሲዳረግ እነሱኑ መልሶ እየለመነና እየተማጸነ፣ ዳቦው የራሱ ሆኖ እያለ ፍርፋሪ ሲጥጡለት ጭራውን እየቆላ እየወደቀ እየተነሣ አመስግኖ መቀበልን ተላምዶ መኖርን ነው ወይ ልናስተምረው የሚገባው? ዘለዓለም ድህና ተመጽዋች፣ የወያኔና የአጋር ባለሀብቶቹ ባሪያ ሆኖ እንዲቀር ነው ወይ ፍላጎታችን?

ይህ የእንቧጭ አረም ጣና ላይ ማን ለምን ዓላማ አምጥቶ እንደዘራው ካሉ ነባራዊ ሀቆች በመነሣት ከሦስት ወራት በፊት "የጣና ችግር ታስቦበት የተደረገ ወይስ የአጋጣሚ!" በሚል ርእስ በጻፍኩት ጽሑፍ ላይ መግለጤ ይታወሳል፡፡ ታዲያ የችግሩ ፈጣሪ እነማን ሆነው ነው እነሱኑ የመፍትሔ አካል አድርገን ልንቆጥርና እኛን ለመሸንገል በሚጥሉት ተደልለን ጭራችንን እየቆላን ልናመሰግን የምንችለው? አገዛዙ ግዴታው እንደመሆኑ እርምጃ መውሰድ ሲኖርበት እንቧጭ አረም መላ ጣናን እስኪያለብሰውና እስከአሁንም ድረስ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስድ እጅ እግሩን አጣጥፎ የተቀመጠው ለምን ይመስላቹሀል? እንዴት ይሄንን በግልጽ የሚታይ ሸፍጥን መረዳት ይሳነናል? አብሶ ደግሞ ወያኔ በየቦታው የዘር ግጭት እየቀሰቀሰ ስንት ወገኖቻችን በገጀራ እየተቀነጠሱ፣ ቤት ንብረታቸው ተቃጥሎ እየተፈናቀሉ ባሉበት ወቅት ምን ያህል የንቃተ ሕሊና ችግር ያለብን፣ አቅለ ቀላልና ተላላ፣ የወገን መከራም የማይቆጨን፣ የማይሰማን፣ የማያሳስበን ብንሆን ነው የወያኔን ዋነኛ ድጋፍ የሆነን ሰው ለማመስገን ለማወደስ ቃላት የሚያጥረን የሆነው? ሌላው ሁሉ ይቅርና ለመሆኑ ጤነኛስ ነን ወይ???

ሸህ አልአሙዲ ማለት ማን ነው? ለእኛ ወይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው አስተሳሰብ ምንድን ነው? አል አሙዲ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአረመኔውና ከወንበዴው፣ ከዘራፊው የወያኔ አገዛዝ ነጻ እንዲወጣ ፈጽሞ የማይፈልግ ክፉ ሰው ነው፡፡ ይሄንን ፍላጎቱን በበርካታ አጋጣሚዎች ግልጽ አድርጓል፡፡ ሁለቱን ለመጥቀስ ያህል አንደኛው በምርጫ 1997 ዓ.ም. "ኢሕአዴግን ምረጡ!" ብሎ የቀሰቀሰበት ሲሆን ሌላው ደግሞ ከዚያ በኋላ "ለሕወሓት/ኢሕአዴግ ነፍሴንም ቢሆን እሰጣለሁ!" ብሎ ሰፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል በሕዝባችን ላይ ሲፈጽም ለቆየና እየፈጸመ ላለ፣ ለጠባብና ጎጠኛ የቡድን ጥቅሙ ሲል የሀገራችንንና የሕዝባችንን አንድነትና ህልውና አደጋ ላይ ለጣለ፣ በዜጎች ላይ ከፍተኛና በርካታ ኢሰብአዊና ዘግናኝ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችንና ሰቆቃዎችን ሲፈጽም ለኖረና እየፈጸመ ላለ አሸባሪ የጥፋት ኃይል "ነፍሴንም ቢሆን እሰጥለታለሁ!" በማለት አገዛዙ በሚቆጣጠረው ብሔራዊ የብዙኃን መገናኛ በመናገር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ንቀትና ጥላቻ፣ ለአገዛዙ ደግሞ ያለውን ታማኝነት አጋርነትና ፍቅር በአደባባይ ያረጋገጠበት ነው፡፡

ይህ ሰው ወያኔ የውጭ ግንኙነት ችግር በገጠመው ቁጥር አል አሙዲ ለበርካታ ጊዜያት ለሎቢዎች (ለአግባቢዎች) እየከፈለ ወያኔን ከአጣብቂኝ ችግር በማውጣት የወያኔ ዕድሜ እንዲራዘም አድርጓል፡፡ ሌላው ቀርቶ በሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያዊያን የሚያደርጉትን የስፖርት (የፍን) ውድድርን እንኳ በወያኔ ቁጥጥር ስር ለመጣል ዶላር በመርጨት ጥረት ያደረገ ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው እንዲህ ዓይነት ክፉ ተግባሮቹን በመፈጸም ለኛ ጠላትነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለእኛ ካለው ንቀት የተነሣ ሊመጻደቅብን፣ ሊሸነግለን፣ ያለ ማስታወቂያ ክፍያ አስተማማኝ የንግድ ማስታወቂያ ለመሥራት፣ በክፉና አስነዋሪ ተግባሩ የጠፋ ስሙን ለማደስ፣ ለመወደስ፣ ለመወደድ ሲል ያደረገውን ፍርፋሪ ጣለ ብየ እንዴት ነው ይሄንን ጠላት የሚያመሰግን ሕሊና ሊኖረኝ የሚችለው? ይህ ግለሰብ ሁለንተናዊ ድጋፍ በሚሰጠው ግፈኛ አገዛዝ ደማቸው የፈሰሰ፣ ደብዛቸው የጠፋ ሕፃናት፣ እናቶች፣ አረጋውያን፣ ሴቶች፣ ወንዶች ወገኖቸ በከንቱ የፈሰሰ ደም ምን ይለኝ??? እንዴትስ ይቻለኛል?

ገንዘቡ ከኛ የተዘረፈ በመሆኑ ይህ ገንዘብ ሲመጣ ስንቀበለው በደስታ ነው፡፡ ምስጋና ግን እንዴት ብለን? ለምኑስ ነው የምናመሰግነው? ከአገዛዙ ጋር ተመሳጥሮ ስለዘረፈን፣ በድህነት ላይ ድህነት በችጋር ላይ ችጋር ስለጨመረልንና ከዘረፈን ላይ ድቃቂ ስለጣለልን ነው ጎሽ ብለን የምናመሰግነው? ነው ወይስ ይሄንን እውነታ መገንዘብ የተሳነን ዘገምተኛ ሆነን ነው ድቃቂ ተጣለልን ብለን ልባችን ጮቤ እየረገጠ ልናመሰግነው የሚገባን??? እነኝህ ግለሰቦች ይሄንን ሰው ሲቃ እየተናነቃቸው ሲያመሰግኑና "አመስግኑ አወድሱ!" ብለውም ለሕዝብ ሲያሳስቡ ምን ማለታቸው እንደሆነ፣ ሕዝቡን እንዲያመሰግን ሲያደርጉት በሕዝቡ ሥነልቡና ላይ ምን እየፈጠሩ እንደሆነ የሚረዱ ሰዎች አይደሉም፡፡

እነኝህ ግለሰቦች ከላይ የገለጽኩላቹህን ነገሮች ለመረዳት የሚያስችል ንቃተ ሕሊና ስለሌላቸው ብቻ አይደለም

እውነታውን ሊረዱ ያልቻሉትና የአል አሙዲ አገብጋቢ ሊሆኑ የቻሉት፡፡ የብሔራዊ ክብር፣ የማንነት፣ የኩራት፣ የሞራል (የቅስም) እሴቶች ወዘተረፈ. ነገር ቢጠበስ የማይሸታቸው፣ ዴንታ የማይሰጣቸው በመሆናቸውም ነው እንጅ፡፡ የእነኝህ እሴቶቻችን ነገር ግድ የሚሰጣቸው ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ድሀ ስለሆንን ብቻ ክብር የማይገባንና ክብር የሌለን እንደሆንን ቆጥሮ ሴቶች እኅቶቻችንን በገንዘቡ ሊገዛቸው እንደሚችል፣ ድሀ ስለሆንን ክብር የሚባል ነገር የማናውቅና ለገንዘብ ስንል የማንሸጠው የማንለውጠው ነገር የሌለን እንደሆነ ሊያሳምነን ጥረት በሚያደርግ አኳኋን፣ ቅስማችንን ሊሠብር በሚችል አቀራረብ በግላጭ በአደባባይ ከሴቶቻችን ጋራ መዋሸሙን እያሳየ፣ ሰብአዊ ክብርን ነፍጎ ንቀት በተሞላበት ሁኔታ እኅቶቻችንን እንደ ዕቃ የሚጠቀምባቸው መሆኑ አገሩ ሁሉ ለሚያውቅበት፣ የሕዝባችንን ክብር በእጅጉ ለተዳፈረ ነውረኛ ሰው ሸንጣቸውን ገትረው ጥብቅና ባልቆሙ ነበረ፡፡ ለነኝህ ሰዎች ጨዋነትና አዋቂነት ማለት እውነትን መናገር፣ አጥፊን መገሰጽና ይታረም ዘንድ ልክ ልኩን መንገር ሳይሆን በምንአገባኝ ስሜት ብልግናንና ግፍን አይቶ እንዳላዩ ማሳለፍና አድርባይነት ነው፡፡

ሸህ አል አሙዲ አመል ካለበት ይሄንን ተግባሩን ሕዝብ በማያውቅበት መልኩ በሸሸግ ማድረግ ሲችል በግልጽ ሆን ብሎ ሰዉ ሊያውቅ በሚችልበት ሁኔታ "እከሊትን ተኛትና እንዲህ አደረገላት!" በሚባልበት ሁኔታ እያደረገ ያለው አውቆ ለዕኩይ ዓላማ ነው፡፡ ቅስማችንን ለመስበር፣ የሐበሻ ሉዓላዊ ማንነታችንን ለመድፈር፣ ክብራችንን ለማዋረድ በማሰብ ነው፡፡

አነኝህ የአል አሙዲ ደጋፊዎች እኅቶቻችን ለሸህ አል አሙዲ ተኝተው ገንዘቡን ካገኙ በኋላ ባለው ሕይዎታቸው ከኅብረተሰባችን በሚሰነዘርባቸው አሸማቃቂ ስድብ ቅስማቸው ተሰብሮ፣ ክብራቸው ተዋርዶ ቀና ብለው ሰው ማየት ተስኗቸው ከሰው ተገልለው ለመኖር መገደዳቸው፣ ክብሩ የተጠበቀ ትዳር መመሥረት የማይችሉበት አስቀያሚ ሕይዎት እንዲገፉ መገደዳቸው፣ ውርደቱ ከእነሱም አልፎ ለቤተሰቦቻቸው መትረፉ ትንሽም የማያሳዝናቸው፣ የማይከነክናቸው፣ የማያሸማቅቃቸው የመከኑ ዜጎች ናቸው፡፡

ለአነዚህ ግለሰቦች ቆነጃጅት እኅቶቻችን "ለሸሁ ሴቶችን ያቀርባሉ፣ ሰውየውን ይግባባሉ" ወደሚባሉ ሰዎች እየተጋፉ መቅረባቸው፣ አንዳንዶችም እኅቶቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ሳይቀር ከሸሁ ጋር አቀላጥፈው ገንዘብ ለማግኘት ሲጥሩ ከማየት ደረጃ ለደረሰ ለሚቀፍ ለሚያሸማቅቅ የሞራል ዝቅጠትና ውርደት መዳረጋችን ምንም ስሜት የሚሰጥ ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን ትንሽም እንኳ ማሰብ የሚችል ጭንቅላት ቢኖራቸው ከዚህ በላይ ምንም ቅስም የሚሠብርና አሸማቃቂ አዋራጅ ነገር እንደሌለ ባወቁ በገባቸውም ነበር፡፡

ወደኋላ እንመለስና ይህ ሰው ለወያኔ "ነፍሴንም ቢሆን እሰጣለሁ!" ሲል ቀልዱን ይመስላቹለል? እንዴትስ ለወያኔ የዚህን ያህል ታማኝ ሊሆን ቻለ ብላቹህ አስባቹህ ታውቃላቹህ? እንዴት ነፍስን እስከመስጠት የሚያደርስ ጥብቅ ቁርኝት ሊኖረው ቻለ? ብላቹህ አስባቹህ ታውቃላቹህ? ይህ ሰው በወያኔ ምን ያህል ተጠቃሚ ቢሆን ነው ይሄን እስከማለት የደረሰው ብላቹህ አስባቹህ ታውቃላቹህ? ይህ ሰው የዚህን ያህል ለወያኔ በመታመኑ በወያኔ ዕድሜ መርዘም፣ ወያኔ በኛላይ በሚያደርሰው ግፍና ሰቆቃ የዚህ ሰው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ አስባቹህ ታውቃላቹህ? ይህ ሰው ለወያኔ "ነፍሴንም ቢሆን እሰጣለሁ!" ሲል ወያኔ በፈጸመው ግፍና ሰቆቃ ሁሉ እስማማለሁ እደግፋለሁ ማለቱ እንደሆነ አስባቹህ ታውቃላቹህ? ነው ወይስ ከላይ እንደጠቀስኳቸው ሰዎች ንቃተ ሕሊናቹህ ደካማ ስለሆነ ይሄ ይሄ ታይቷቹህና ታስቧቹህ አያውቅም???

ሸህ ሙሐመድ ሐሰን አል አሙዲ መቸ ወደሀገራችን እንደገባ ታስታውሳላቹህ? ከወያኔ ጋር ነበር አብሮ የገባው፡፡ ያኔ ሀገሪቱ እንኳንና መዋዕለ ንዋይ ለሚያፈስ ባለሀብት ዜጎች እንኳ ክንፍ ቢኖራቸው በረው በረው የትም ጥፉ ጥፉ የሚል አስፈሪ አሥጊ ድባብ ነግሦ በነበረበት ወቅት ነበር ሰውየው ወደሀገራችን የገባው፡፡ ለምን? እንዴት? ብላቹህ ጠይቃቹህ፣ አስባቹህና መርምራቹህ ታውቃላቹህ?

* ይህ ሰው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሆነው የሌላ ሀገር ዜጎች ለሆኑ ባለሀብቶች ክልክል የኢንቨስትመንት (የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት) ዘርፍ በሆነ ለምሳሌ የወርቅ መዓድን የማውጣት ሥራ መሥማራት ለባዕዳን ተወላጆችና የውጭ ዜግነት ላላቸው

ኢትዮጵያውያን በሕግ ክልክል በሆነበት ዘመን ለእሱ ተፈቅዶለት እንደልቡ እያወጣ ሲያግዝ የነበረ ሰው ነው ለምን???

* አንድ ባለሀብት በባንክ (በቤተ ነዋይ) እና በኢንሹራንስ (በዋስትና) ዘርፎች በአንደኛው ብቻ እንጅ በሁለቱም ላይ መሠማራት እንደማይችል የሚከለክል ሕግ እያለ ለእሱ ግን ተፈቅዷል ለምን???

* ሸህ አል አሙዲ ዜግነቱ ሳውዲዓረቢያዊ ነው፡፡ ለውጭ ዜጋ በባንክ ዘርፍ መሠማራት ክልክል ሆኖ እያለ ለሱ ግን ተፈቅዷል ለምን???

* ሌሎች ዜጎች ለግንባታ፣ ለልማት የያዙትን ቦታ "በሕጉ መሠረት መገንባት፣ ማልማት በሚገባቹህ ሰዓት አልገነባቹህም፣ አላለማቹህም!" ተብለው ቦታቸውን ሲነጠቁ እሱ ግን ለወራት አይደለም ከሃያ ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ ቦታዎችን አጥሮ ሲያስቀምጥ ማንም ምንም የሚለው የለም፡፡ ሕግ በሱላይ ተፈጻሚ አይደለም፣ በሕገወጥ መንገድ ነው ሀብት እያጋበሰ ያለው፡፡ ብቻም ሳይሆን ሥራውን የሚሠራው ከብሔራዊ ባንክ በተገኘ ብድርም ነው ለምን???

* ዩራኒየምን ጨምሮ በሀገራችን መኖራቸው የማይታወቁ የነበሩ እጅግ ውድ የሆኑ የከበሩ መአድናት በሀገራችን በተለያዩ ሥፍራዎች ያውም በቀላሉ በገበሬዎች እየተገኘ ምንነቱ ተጣርቶ ሲታወቅ የተገኙባቸው ቦታዎች ይታጠሩና በወታደር እየተጠበቁ "ለአል አሙዲ ተሰጥቷል!" እየተባለ በአካባቢው ሰው እንዳይደርስ እየተደረገ ከሰው ዕይታ ውጭ በሆነ ሁኔታ መአድናቱ እንዲወጡ እየተደረጉ ሲጋዙ እየታየ የሀገሪቱን የመዓድናት ወጪ ንግድ የሽያጭ ዝርዝርን በምታዩበት ወቅት ግን እነኝህን መዓድናት ከዝርዝር ውስጥ ብትፈልጓቸው አታገኙዋቸውም፡፡ ለምን? ብላቹህ ጠይቃቹህና መርምራቹህ ታውቃላቹህ???

* ..... በርካታ መጣራት የሚፈልጉ ጥሩና ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች በዚህ ሰው ዙሪያ አሉ ለምን???

ለምን? ለሚሉ ጥያቄዎች መልሱ የሚመስለኝ ከሸህ አልአሙዲ ሀብት ወያኔ ከፊል ድርሻ ስላለው ወይም ወያኔ የአል አሙዲ ባለሀብትነቱን በሽፋን ለመጠቀም ስለፈለገ ስሙን ተከራይቶት ወያኔ በሰውየው ስም እየነገደ ሀብት እያጋበሰ ስለሆነ ይመስለኛል፡፡ ይሄንን ጥርጣሬ የሚያጠናክረው እጅግ የጠበቀ ወዳጅነታቸው፣ አጋርነታቸው ብቻ ሳይሆን ባለሀብት ፈጽሞ ሊገባ በማይችልበት ሀገሪቱ ፈጽሞ ባልተረጋጋችበት አስፈሪ ድባብ በነገሠበት ዘመን ሰውየው አብሮ ከወያኔ ጋር መግባቱ ነው፡፡

ባለሀብቶች በአንድ ሀገር ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ሲያስቡ በቅድሚያ የሚመለከቱት ነገር ሀገሪቱ የፖለቲካ መረጋጋት ያላት ሀገር ናት ወይ? ወይም የተረጋጋችና ሰላም ያላት ሀገር ናት ወይ? መንግሥቷስ ሕዝባዊ ተቀባይነት ያለው መንግሥት ነው ወይ? የሚለውን ነገር ነው፡፡ ይህ ምኅዳር በሌለበት ሀገር መዋዕለ ንዋይ ቢያፈሱ በሆነ አጋጣሚ ለኪሳራ ሊዳረጉ፣ ያፈሰሱትን ሀብት ሊያጡ እንደሚችሉ ስለሚያውቁ በእንደዚህ ዓይነት ሀገር ማንም ባለሀብት መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ አይፈልግም፡፡ ሸህ አል አሙዲ ግን ፈጽሞ በማይጠበቅ መልኩ ከዚህ ነባራዊ ሀቅና የባለሃብቶች እሳቤ ውጭ በሆነ ሁኔታ ነበር በቀውጢ ሰዓት የገቡት፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከላይ የገለጽኩላቹህ ይመስለኛል፡፡ እንግዲህ ከላይ በገለጽኩላቹህ መልኩ በአደባባይ በሕዝብ በሚታዩ ነገሮች ላይ ያለ አንዳች የተጠያቂነት የኃላፊነት ስሜትና መሸማቀቅ በሕገወጥ መንገድ እየሠሩ (እየዘረፉ) ያሉ አገዛዙና ባለሀብቱ ሕዝብ በማያየው ጉዳይ ላይ ለሕግ ታማኝ ሆነው የሚሠሩ ይመስላቹሀል ወይ? ቂል ካልሆናቹህ በስተቀር አዎ እንደማትሉኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡

እናም ሸህ አልአሙዲ ለተቸገሩ ገንዘብ የሚሰጥበት ምክንያት ያለ ማስታወቂያ ክፍያ አስተማማኝ የንግድ ማስታወቂያ ለመሥራት፣ በአስነዋሪ ምግባሩ ያደፈ የጎደፈ ስሙን ለማጽዳት፣ አስነዋሪ ምግባሩን ለመሸፈን፣ በሕዝብ ዘንድ ለመወደስ፣ ተወዳጅነትን ለማግኘት፣ አመኔታን ለማትረፍ፣ ለመሸንገል፣ ለመደለል፣ ለመመጻደቅ ወዘተረፈ እንጅ ፈጽሞ ለተቸገሩ ወገኖቻችን በማዘን እንዳልሆነ መቶ በመቶ ላረጋግጥላቹህ እወዳለሁ፡፡ ምክንያቱም ሰውየው በ21ኛው መቶ ክ/ዘ በአረመኔነቱ ተወዳዳሪ የሌለውን አረመኔያዊ አገዛዝ አፍቃሪና ነፍሱን እስከመስጠት ድረስ አጋር ደጋፊ የሆነ ጨካኝ ሰው፣ የዚህን ደሀ ምስኪን አሳዛኝ ሕዝብ ሀብት ከአገዛዙ ጋር ሆኖ በገፍ እየዘረፈ ያለና በደሀ ሕዝብ ላይ የጨከነ ዘራፊ ሰው

በምንም ተአምር ቢሆን በውስጡ ርሕራሔና ሐዘኔታ ልቡ ውስጥ ሊሰማው አይችልምና ነው፡፡ አሁንም መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኘ የምነግራቹህ ይህ ሰው ልቡ ውስጥ ጥቂትም እንኳ ሐዘኔታና ርሕራሔ ቢኖረው ኖሮ ደማችንን እየጠጣ ያለውን አረመኔ፣ ኢሰብአዊ፣ ወንበዴ ዘራፊ የሆነውን ወያኔን የሚረዳ፣ የሚያፈቅር፣ የሚደግፍ አይሆንም ነበረ፣ ይሄንን በድህነትና በችጋር እየማቀቀ ያለውን የዓለማችንን ምስኪን ደሀ ሕዝብ ከወያኔ ጋር አብሮ አይዘርፍም ነበረ፡፡

ብዙዎቻቹህ ይሄንን ጽሑፍ ስታነቡ "አይ ይሄ ሰው በቃ ሽሁ የገቡትን ቃል እንዲያጥፉት አደረገብን!" ልትሉ እንደምትችሉ እገምታለሁ፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደጠቆምኳቹህ ሰውየው ይሄንን የሚያደርግበት የራሱ ዓላማ አለውና ያስቀርብናል ብላቹህ አትሥጉ፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን በችግሮቻችን ጊዜያዊ መፍትሔ ላይ ከማተኮር ወጥተን በጣና፣ በሀገራችን፣ ባጠቃላይ በሕዝባችን ላይ ተነግረው የማያልቁ ችግሮችን የፈጠረውንና ወደፊትም ለመፍጠር ቁርጠኛ የሆነውን የወያኔን አረመኔ የጥፋት ኃይል በተቻለ ፍጥነት ልናስወግድ በምንችልበት ጉዳይ ላይ ማተኮርና መረባረብ ነው ያለብን፡፡ ይሄንን ማሰብ ካልቻልን ግን ወያኔ እንደ እንቧጭ ያሉ ሌላ ነገር እንዳናስብ ኃይላችንን፣ ጊዜያችንን፣ ገንዘባችንን እዚያ ላይ እንድናጠፋ እንድናባክን የሚያደርጉ በርካታ ችግሮችን በየደጃችን እየፈጠረ ቀና ብለን እንዳናየው በማድረግ ዘለዓለም ቀጥቅጦ ሲገዛህ መኖሩ ነው፡፡

ወገን ሆይ ፈጥነህ ንቃ! ወዳጅ ጠላትህን ለይተህ ዕወቅ! የመርሕ ሰዎች እንሁን እንጅ ማንም እያጃጃለ የሚቀልድብንና በማይረባውም በሚረባውም የምንደለል አንሁን! ዓላማና ግብ የሌለው የእውር ድንብስ ጉዞ አንጓዝ! ስለነገ እናስብና ነገን እንደምንፈልገው ለማድረግ በርትተን እንጣር! በተግባራዊ እንቅስቃሴ እንጅ በምኞት ብቻ ምንም የሚሆን የሚለወጥ ነገር የለምና!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!
ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com